# በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ላይ የተቃጣው አደጋ ተጠናክሮ ቀጥሏል!

## <u>ከወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ የሰብዓዊ መብት ድርጅት የተሰጠ መግለጫ፤</u>

ባሳለፍናቸው ተከታታይ ወራት የወልቃይት ጠገዴን ሕዝብ መከራና ስቃይ በመጠኑም ቢሆን ለማሣየት በምናደርገው ጥረት ሕዝባችን እራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱ ይከበርለት፣ እንድንገባ ከተገደድንበት የማንነት ቀውስ ውስጥ ለመውጣት የሚደረገው ትግል ምላሽ ያግኝ፣ ቢያንስ በሕገ-መንግሥቱ ከተቀመጡ ሰብዕዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አንፃር ጥያቄዎቻችን መልስ ያግኙ፣ የአካባቢያችን ተወካይ ለወከላቸው ሕዝብ ድምፅና ጥሪ ይቁሙ፣ ወዘተ... በሚል ተከታታይ መግለጫዎችን ስናወጣ መቆየታችን አይዘነጋም።
ዛሬም እነሆ በሕዝባችን ላይ የተቃጣው አደጋ ተባብሶና ተጠናክሮ ቀጥሏል።

የሕወሓት ሃብቶች ውስጥ ከሆኑት አንዱ የሆነው ሒዎት ሜካናይዝድ የተባለው በእርሻ ላይ የተሠማራ ድርጅት ከግማሽ የማያንስ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራን መሬት ተቀራምቶ፣ በዚሁ መሬት ላይ ክልል አንድ (የትግራይ ክልል) የአካባቢውን ተወላጆች በማፈናቀል ከአራት-መቶ ሽህ በላይ የትግራይ ተወላጆችን አስፍሮ፣ የአካባቢው ተወላጆች ሰብአዊና የዜግነት መብቶቻቸው ተገፎ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲቆጠሩና በተራ የጉልበት ሥራ ላይ አገልጋይ እንዲሆኑ፣ ከብቶቹን እንኳ የሚያሰማራበት መሬት አጥቶ እንዲንገላታ፣ እንዲሰቃይና እንዲፈናቀል እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል።

በቅርቡ ደግሞ ክልል አንድ (የትግራይ ክልል) ከግብርና ውጭ በሌላ ለመሠማራት ዕድልና አቅም የሌለው ድሃ ወገናችንን መድረሻና መተንፈሻ ለማሣጣት ብሎም አጠቃላይ ተፈናቃይ ለማድረግ ባለው ቀጣይ እቅድ መሠረት የሸኽ መሐመድ አላሙዲን ንብረት የሆነ በእርሻ ሥራ ላይ የሚሠማራ የኤኮኖሚ ተቋም በአካባቢው ለማንቀሣቀስ ሥራ መጀመሩን የደረሰን መረጃ ያረጋግጣል።

የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን እስካሁን ድረስ አሜሪካ በሚገኘው ኤምባሲም ይሁን በክልል አንድ ተወካዮችና መልእክተኞች የሚሰጠው ገብታችሁ አካባቢያችሁን አልሙ የሚል ድለላ እውነት እየመሰለው ከፍተኛ የሆነ ጥሪታቸውን ወደ አገር በማስገባት ንብረታቸው በከንቱ እንዲወድም በመደረጉ የሕዝባችን ስሜት ጭራሹን እንዲጎዳ ተደርጓል። ይህ ሁሉ ሆኖ ዛሬ ደግሞ ይባስ ተብሎ ጭራሽ የአካባቢው ሕዝብ የባለሃብቶች ጥጥ ለቃሚና በጉልበቱ አገልጋይ እንዲሆን ብቻ በማሰብ የክልል አንድ ሃላፊዎች ሴራቸውን በመቀጠል እነሆ በሌላ የልማት ሥራ መሠማራትና እራሣቸውንና ወገናቸውን መጥቀም የሚችሉትን ባለ ሃብት ሸኽ ሙሐመድ አላሙዲን የስህተት ተባባሪ ለማድረግ መወሰኑ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ተወላጅ ኢትዮጵያውያንን እጅጉን ያሳዘነንና ያስቆጣ ጉዳይ ነውና ድርጊቱ ተፈፃሚ ከመሆን እንዲቆም አጥብቀን እንጠይቃለን።

በኛ በኩል ባለሃብቱ ወገናችን ሸክ መሐመድ አላሙዲን በዚህ ባልተጠናና የአካባቢውን ሕዝብ ተፈናቃይ በሚያደርግ ተግባር ላይ አውቀው የገቡበት ነገር ነው ብለን በአሁኑ ጊዜ ማመን አንችልም።
የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ በትራክተር ሲጠቀምና መሬቱን ሲያለማ በትውልዶች የሚቆጠር ዓመታት ያሳለፈ ሕዝብ በመሆኑ ሌሎች በአዲስ መልክ የእርሻ ልማትንና በትራክተር መጠቀምን እንደ አዲስ የልማት ሥራ የሚያስተዋውቁት ሕዝብ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የሚገርመው አካባቢውን ለማልማት በሚል ሰበብ ሽፋን የሚሆን ድጋፍ ለማግኘት ታስቦ የክልል አንድ ተወካዮች ኮሎምበስ፣ ኦሃዮ ድረስ መጥተው የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች

አካባቢያችሁን እንድታለሙ የራሳችሁ የሆነው መሬት እንዲሰጣችሁ አመልክቱ ተብለው ማመልከቻ ካቀረቡ አሥር ሽህ በውጭ የሚኖሩ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ተወላጆች ውስጥ የገኘው ፓርቲ የሕወሓት አባል ወይም ደጋፊ ናቸው ብለው ላመኗቸው ከስምንት ለማይበልጡ ግለሰቦች ብቻ መሬት መሰጠቱ የአካባቢው ተወላጅ በሆኑ ስደተኛ ኢትዮጵውያን ላይ እንደተፈዘና ድሮም ዓላማው የአባልነትና የድጋፍ መግዣና መደለያ እንዲሁም በአካባቢው ተወላጆች መኻል መከፋፈልን ለመፍጠር ታስቦ የተደረገ ተንኮል እንደሆነ ይበልጥ ግልፅ ነው::

መሬት ተሰጣቸው ከተባሉት ሰዎችም መካከል ከሁለትና ሦስት ትራክተሮች በላይ ላስገቡ ሦስት ወገኖቻችን ከፍተኛው 50 እና 100 ሄክታር መሬት ብቻ እንደተሰጣቸውና አንዳንዶቹም ውስጠ ምስጢሩ ገብቷቸውና በጉዳዩ አዝነው የልማት ሥራ የተባለውን ቀልድ ጭራሹን ትተዋል:: እነዚህ ወገኖቻችን የወሰዱትን ቆራጥ እርምጃ ድርጅታችን ያደንቃል:: መጀመሪያውኑም የክልል አንድ ዓላማ በወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ለሚከተለው ጎጅ ፖሊሲ የአካባቢው ሕዝብም ተሣታፊ ነው ለማሰኘት በሽፋንነት የሚያገለግሉት አንዳንድ ተባባሪዎችን ለማግኘት፣ የራሱን መሬት በመስጠት የገኘው ፓርቲ አባልና ተባባሪ እንዲሆን ለማድረግና በዚህም በተወላጁ መካከል ክፍፍልን ለመፍጠር የታሰበ ተንኮል እንጅ እውነት ተወላጁ ሕዝብ እንዲጠቀም ታስቦ እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: ይህንን ደግሞ ከማንም ይበልጥ የአካባቢው ተወላጆች ጠንቅቀን የምናውቀው ጉዳይ ነው::

በውጭ የሚኖሩ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ተወላጆች ውስጥ የተወሰኑ ወገኖቻችን የአካባቢው ተወላጆች ገብታችሁ መሬታችሁን አልሙ፣ ተጠቀሙ የሚለውን ድለላ በቀና መንፈስ ተቀብለውና በክሬዲት ካርድ (በብድር) ሣይቀር ገንዘባቸውን አውጥተውና ንብረታቸውን ከስክሰው ሰላሣ የእርሻ መኪናዎችን (ትራክተሮችን) በ2000 ዓ/ም. (2007 እ.አ.አ.) አስገብተው ዛሬ ድረስ ጥቅም ላይ ሳይውሉ ዝገው፣ ዳዋ ለብሰውና እንዳልነበሩ ሆነው እንዲቀሩ መደረጉ በጣም ያሳዘነን ብቻ ሣይሆን የሚያስጠይቅ ጉዳይ ነው:: ሌላው ቀርቶ የአካባቢው ተወላጆች ገብተው መሬታቸውን እንዲያለሙ የክልል አንድ ተወካዮች ያንን ሁሉ ድለላና ስብከት ካደረጉ በኋላ ወገኖቻችን ገንዘባቸውን አውጥተው የገዟቸው ትራክተሮች ጅቡቲ ላይ ታግተው ለማስገባት ከፍተኛ ችግር በገጠማቸው ጊዜ የክልል አንድ ሃላፊዎች እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ያደረጉት ልመናና ተማፅኖ ጭራሽ አድማጭ ሣያገኝ ቀርቶ መጨረሻ ክልል ሦስት (የአማራው ክልል) ባደረገው ትብብርና እርዳታ ነው ንብረታቸውን ማስለቀቅና ወደ ወልቃይት ጠገዴ ማስገባት የተቻለው:: በዚህ አጋጣሚ ቀና ትብብር ላደረጉልን የክልል ሦስት (ብአዴን) ሃላፊዎች ላደረጉልን ወገናዊ እርዳታ ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን::

በውጭ የምንኖር የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራችን ገብተን ልማት ሥራ ላይ እንድንሠማራ እዚህ ሰሜን አሜሪካ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የአሜሪካ ዜግነት ላላቸው ወገኖች የኢትዮጵያዊነት መታወቂያ ተብሎ የሚሰጠውን ብጫ ወረቀት ለማግኘት ከእያንዳንዱ የአካባቢው ተወላጅ አምስት መቶ የአሜሪካ ዶላር ሲሰበሰብ ቆይቷል:: ያም ሆነ ግን ክፍያ ለመሰብሰብ የሚቀላጠፈው ኤምባሲ የአካባቢው ተወላጆች የደረሰባቸውን እክልና ችግር አስመልክቶ የሚመለከታቸውን የመንግሥት ክፍሎች እንዲጠይቅና መልስ እንዲሰጥ ትብብርም እንዲያደርግ በተደጋጋሚ ላቀረብናቸው ጥያቄዎችና ማሳሰቢያዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አንዳችም መልስ አለመስጠቱና ዜጎቹን ለማገልገል ባለቻሉ አሳዝኖናል:: ይኸንን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ችላ ባይነትና ሃላፊነት መዘንጋት በተመለከተ ድርጅታችን ስለሚወስደው ሕጋዊ እርምጃ ወደፊት እንገልፃለን::

ባለሃብቱ ሸኽ መሐመድ አላሙዲን የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራን ገበሬ ሊጠቅሙና ኑሮውንም ሊለውጡ በሚችሉ ለውጭ ምንዛሬም ሆነ ለአካባቢው ሕዝብ በሚጠቅሙ የቴክኖሎጂ ሥራዎች ላይ ለምሳሌ ገበሬው ለሚያመርታቸው እንደ ሰሊጥ ለመሣሰሉት

የቅባት እህሎች የዘይት ፋብሪካ ወይም ሕዝቡ ለሚያመርተው ጥጥ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሊያቋቁሙሉት ወይም ሌሎች የቴክኖሎጂ ሥራዎችና የልማትና የንግድ ሥራዎች ላይ በመሠማራት ሕዝባችንንም ሆነ እራሣቸውን መጥቀም በሚችባቸው መስኮች እንጂ ክልል አንድ ሆን ብሎ በያዘውና በተሠማራበት ድሃ ገበሬን በሚያፈናቅል፣ በሚያሳድድና መድረሻ በሚያሳጣ አሳዛኝ ሥራ ውስጥ እንዳይገቡና ተባባሪ እንዳይሆኑ እናሳስባለን፡፡

የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሰብዓዊ መብት ድርጅት አሁንም ቢሆን ማንኛውም የአካባቢው ተወላጅ በልዩ ልዩ ምክንያቶችና በመካከላችን ልዩነት እንዲኖር ክልል አንድ በሚፈጥራቸው ሰበብ አስባቦች ሳይከፋፈል አንድነቱን ይበልጥ አጠናክሮ ለመብቱ መከበር የሚያደርገውን ሰላማዊ ትግል ከመቀጠል ሌላ አማራጭ የለውም ብሎ ያምናል፡፡

በድጋሜ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለሰው ልጆች መብት የቆማችሁ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ወገኖች ሁሉ ይህ ሥር ነቀል የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲቆም በምናደርገው ሰላማዊ ትግል ከጎናችን እንድትሰለፉና ድምፃችሁን ከኛ ጋር እንድታሰሙ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ የሰብዓዊ መብት ድርጅት ወገናዊ የድረሱልኝ ጥሪውን በአካባቢው ተወላጅ ሕዝብ ስም በድጋሜ ያስተላልፋል፡፡

የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ ታሪካዊ ማንነትና መብት ይከበር!

የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሰብዓዊ መብት ድርጅት

ሰኔ፣ 2001 ዓ/ም
ሰሜን አሜሪካ

***(ማሳሰቢያ፡- ቀደም ሲል በዚህ ጉዳይ ላይ ረዘም ላለ ጊዜ ልዩ ልዩ መግለጫዎችን በተከታታይ ሲሰጥ የቆየውና የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች በሰሜን አመሪካ በመባል ይታወቅ የነበረው ድርጅት የወቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሰብዓዊ መብት ድርጅት በሚል ሕጋዊ መጠሪያ መቀየሩን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡)***